# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት

# ኢንስቲትዩት

## የ2009 በጀት ዓመት የኤክስፖርት ድጋፍ ዕቅድ

ሰኔ 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ፤ ........ 3

**ክፍል አንድ፡- የመነሻ ሁኔታዎች፤** ........ 4

1.1. በማክሮ ደረጃ የተቀመጡ መነሻዎችና ዓላማዎች፤ ........ 4

1.2. የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፤ ........ 4

1.3. የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ጥቅል ዓላማዎችና የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች፤ ........ 5

**ክፍል ሁለት፡- የ2008 በጀት ዓመት የኤክስፖርት አፈፃፀምን በተመለከተ፤** ........ 7

2.1. የኤክስፖርት አፈፃፀም ያለበት ሁኔታ፤ ........ 7

2.2. ለአፈፀፀም ጉድለቱ ዋነኛ መንስኤዎች /ማነቆዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች፤ ........ 7

2.3. በቀጠይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤ ........ 14

**ክፍል ሦስት፡- ለ2009 በጀት ዓመት የተያዘ የኤክስፖርት ገቢ ግብ፤** ........ 15

3.1. የዕቅዱ ዓላማዎች፣ ግቦች እና ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት፤ ........ 15

3.2. የ2009 በጀት ዓመት የወጪ ንግድ ዕቅድ በየምርት ዓይነቱ በመጠን፣ በዋጋ እና ታሳቢ የተደረጉ አንኳር ጉዳዮች፤ ........ 26

3.3. ዝርዝር የኤክስፖርት መጠንና የገቢ ግብ ዕቅድ፤ ........ 27

## መግቢያ፤

አገራችን ከድህነት ተላቃ አስተማማኝ የዕድገት ደረጃ ላይ መድረስ የምትችለው የዳበረ ኢንዱስትሪ ሲገነባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ የኢንዱስትሪ ልማት ከሌሎች የልማት መስኮች በላቀ ፍጥነት መከናወንና ማደግ እንዳለበት በመግባባት ርብርብ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በመጀመሪያው የዕቅድ ትግበራ ዓመትም ምንም እንኳን ለቀጣይ ሥራዎቻችን መሠረት ሊሆኑን የሚችሉ ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም በልማት ዕቅዱ የተያዙ ዓመታዊ ግቦችን በአግባቡ ከማሳካት አኳያ የአፈፃፀም ጉድለቶች ነበሩ፡፡ በመሆኑም በተለይ በቀሪዎቹ አራት የዕትዕ ዓመታት ባለፋው አንድ የትግበራ ዓመት የተመዘገቡ ውጤቶችንና በአፈፃፀም ሂደት የተገኙ ተምክሮዎችን መነሻ በማድረግ የተለየ ጥረትንና የተሻለ ውጤትን ማስመዝገብ ካልተቻለ በዋነኛነት በሁለተኛው የዕትዕ ዓመታት ከንዑስ ዘርፉ የሚጠበቀውን እመርታዊ የልማት ዕድገት በአግባቡ ማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሠረት በቀጣዩ የ2009 በጀት ዓመት ከንዑስ ዘርፉ የተሻለ አፈፃፀምና አጠቃላይ የልማት ዕድገት ጋር በተያያዘ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የማይተካ ድርሻ ያላቸውን የልማት ኃይሎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በሙሉ በየደረጃው በማስተባበርና አጠቃላይ ንቅናቄን በመፍጠር የንዑስ ዘርፉን አፈፃፀም ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ይህን መሠረታዊ ምክንያት መነሻ በማድረግም በ2009 የበጀት ዓመት ከቆዳው ንዑስ የኢንስትሪ ዘርፍ 272.7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳካት ግብ ተጥሏል፡፡

በዕቅድ ዓመቱ የተያዘውን የኤክስፖርት ገቢ ግብ በአግባቡ በማሳካቱ ሂደትም በዋነኛነት ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ተቋማዊ የማስፈፀምና የመፈፀም አቅምን የበለጠ አጠናክሮ ከማጎልበቱ ጎን ለጎን በውጫዊ ተግዳሮቶች ላይ በጎ ተፅዕኖን ሊያሳድሩ የሚችሉ ቅንጅታዊ ሥራዎችን በአግባቡ አቅዶ ማከናወን እንደሚገባ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

## ክፍል አንድ፡- የመነሻ ሁኔታዎች፤

### 1.1. በማክሮ ደረጃ የተቀመጡ መነሻዎችና ዓላማዎች፤

በመንግስት በኩል ባለፉት ዓመታት የተፈጠረውን ምቹ (የተረጋጋ) የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ በማዝለቅ በሁለተኛው የዕትዕ ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ በአማካኝ ከ 10 በመቶ በላይ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥና እ.ኤ.አ በ2025 አገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ ታልሟል፡፡ ይህን አገራዊ የልማት ራዕይ በአግባቡ በማሳካቱ ሂደትም በአገር አቀፍ ደረጃ ከተቀመጡ መነሻዎች መካከል አንዱና ዋነኛው፡- ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ የኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማትን በማረጋገጥ ኢንዱስትሪው ከአጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ሊይዝ የሚገባውን ድርሻ በአግባቡ ከማሳደግ ባሻገር የማምረቻ ኢንዱስትሪውን የላቀ ኢኮኖሚያዊ ድርሻ በማረጋገጥ በአገሪቱ ኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግርን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከነዚህ መሠረታዊ መነሻዎች በመነሳትም የሚከተሉት ሁለት ዓላማዎች ለ2009 በጀት ዓመት የኤክስፖርት ዕቅድ ዝግጅት በመነሻነት ተወስደዋል፡-

- የማምረቻ ኢንዱስትሪውን ቀጣይነት ያለው ፈጣንና አስተማማኝ ልማት እውን በማድረጉ ረገድ የሚደረገውን ሁለንተናዊ ጥረት የበለጠ አጠናሮ በማስቀጠል በዕቅድ ዓመቱ በአማካኝ የ24 በመቶ እድገትን ማረጋገጥ፤
- የማምረቻ ኢንዱስትሪው አገራዊ የምርት ዋጋ መጠን ድርሻ በ2012 ወደ 8በመቶ ከፍ እንዲል ማድረግ የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው፤

### 1.2. የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፤

ባለፉት አስርና ከዛ በላይ ዓመታት ሁሉም በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በአገር አቀፍ ደረጃ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነዱ በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ መርህ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀና የዓለም አቀፍ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ሲሆን፤ ዋነኞቹ /ሰባቱ/ የልማት ስትራቴጂው የመነሻ መርሆዎችም የሚከተሉት ናቸው፡-

- የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂው ሞተር የግል ባለሀብት መሆኑን መቀበል፤
- ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል፤
- ኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል፤
- ጉልበትን በሰፊው በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ ያተኮረ የልማት አቅጣጫን መከተል፤
- የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብትን አቀናጅቶ የመጠቀም አቅጣጫ መከተል፤
- መንግስት ጠንካራ የአመራር ሚና የሚጫወትበትን አቅጣጫ መከተል፤ እንዲሁም
- መላው ህብረተሰብ ለኢንዱስትሪ ልማት በጋራ የሚሰለፍበትን አቅጣጫ መከተል፤የሚሉት

የልማት ስትራቴጂው የመነሻ መርሆዎች ናቸው፡፡

## 1.3. የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ጥቅል ዓላማዎችና የማስፈፀሚያ አቅጣጫዎች፤

ከላይ የተመለከቱትን መነሻዎች መሠረት በማድረግም የቀጣዩ ዓመት የልማት ዕቅድ የሚከተሉት መሠረታዊ ዓላማዎች አሉት፡-

1. የንዑስ ዘርፉን ሁለንተናዊ የመፈፀም አቅም በማጎልበት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በመጠን፣ በአይነት እና በዋጋ በማሳደግ በልማት ዕቅድ ዘመኑ የመጨረሻው ዓመት የተያዘውን የኤክስፖርት ገቢ ግብ ማሳካት፤
2. በመካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ከሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በተጨማሪ፤ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የሚሰጠውን ትኩረትና ሁለንተናዊ የአቅም ግንባት ድጋፍ ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክሮ በማስቀጠል በ2009 በጀት ዓመት የንዑስ ዘርፉ ምርት ከአጠቃላይ አገራዊ የምርት መጠን ውስጥ ቢያንስ በአማካኝ የ0.33 በመቶ ድርሻ እንዲይዝ የታቀደውን አገራዊ ግብ ማሳካት፤
3. የላቀ የቴክኖሎጂ ብቃትንና የምርትና ምርታማነት አቅምን በከፍተኛ ደረጃ ሊያሳድጉ የሚችሉ አዳዲስ ኢንቨስትመነትን ወደ ንዑስ ዘርፉ ሥራ በማስገባት ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ ልማትን ማረጋገጥ፤
4. የአካባቢ ጥበቃ አቅምን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ቀጣይነት ያለው ዘለቄታዊ ልማትን ማረጋገጥ፤
5. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለንዑስ ዘርፉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት የጎላ ፋይዳ ካላቸው አካላት ጋር የሚከናወኑ ቅንጅታዊ ሥራዎችን የበለጠ አጠናክሮ በማስቀጠል ለዘርፉ ልማት ራዕይና ዓላማ መሳካት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤

የ2009 በጀት ዓመት የልማት ዕቅድ ፈጣን፣ ቀጣይና አስተማማኝ ዕድገትን በማረጋገጡ ሂደት ከፍተኛ የሆነ አመርታዊ ለውጥ የሚመዘገብበት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ይህንኑ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ መሠረታዊ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተመልክቷል፡-

1. በየደረጃው ፈጣን፣ ቀጣይና አስተማማኝ የእሴት ጭማሪ ዕድገትን ማረጋገጥ፤
2. በውጭ ገበያ የምርት ብዛት፣ ስብጥርና ጥራትን ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ፤
3. ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የሚሰጠውን ሁለንተናዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ አጠናክሮ ማስቀጠልና ውጤታማነቱንም ማረጋገጥ፤
4. ከአካባቢ ጥበቃ ሥራ ጋር የተጣጣመና የተቀናጀ ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ፤
5. የአገር ውስጥና የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፉ ማድረግ፤
6. የደጋፊ ተቋሙን ሁለንተናዊ የድጋፍ አቅም ማሳደግ፤

7. የኢንዱስትሪውን ሰላም ማረጋገጥ፤
8. የጥራት ደረጃውን ያሟላ፣ ያልተቆራረጠ፣ በቂና ፈጣን የምርት ግብዓት አቅርቦት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ፤
9. አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የምርት መዳረሻ ገበያዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፤
10. በጉምሩክ አሰራር፣ በፋይናንስ፣ በትራንስፖርትና በመሳሰሉት ረገድ ፈጣን፣ ግልፅ፣ ፍትሀዊና ተደራሽ አገልግሎት እንዲረጋገጥ ማድረግ፤
11. የስርዓተ-ፆታ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዲሁም የአካባቢ ብክለት ጉዳዮችን በአግባቡ የሥራ አካል በማድረግ፤ የሴቶችና የወጣቶች ብቃትና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

## ክፍል ሁለት፡- የ2008 በጀት ዓመት የኤክስፖርት አፈፃፀምን በተመለከተ፤

**ሠንጠረዥ1፡-** <u>የ2008 በጀት ዓመት የኤክስፖርት ዕቅድ አፈጻጸም</u>፤

| ተ.ቁ | የምርቱ ዓይነት | የ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ2008 በጀት ዓመት አፈጻጸም | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2 | ቆዳና የቆዳ ውጤቶች | 185,000.00 | 116,307.80 | 62.87 |
| 2.1 | ያለቀለት ቆዳ | 109,881.10 | 73,570.36 | 66.95 |
| 2.2 | ጫማ | 67,994.56 | 34,642.72 | 50.95 |
| 2.3 | የቆዳ ጓንት | 6,678.14 | 6,489.94 | 97.18 |
| 2.4 | የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች | 446.20 | 1,604.77 | 359.65 |

### 2.1. የኤክስፖርት አፈፃፀም ያለበት ሁኔታ፤

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ዓመት ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ የኢንዱስትሪ ዘርፍ 185 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 116.307 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙ የዕቅዱን 62.87 በመቶ ነው፡፡ ይህም ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ተገኝቶ ከነበረው የ132.86 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ጋር ሲነፃፀር የ16.55 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (12.46%) ቅናሽ አሳይቷል፡፡

### 2.2. ለአፈፀፀም ጉድለቱ ዋነኛ መንስኤዎች /ማነቆዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች፤

**ሀ) የገበያና ተያያዥ የዋጋ አፈፃፀም ውስንነቶች፡-** በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ለተስተዋለው የምርትና ምርታማነት እንዲሁም የኤክስፖርት አፈፃፀም ጉድለት ተጠቃሽ ከሚሆኑ ምክንያቶች መካከል የጎላውን ድርሻ የሚወስደው ባለቀለት ቆዳ በኩል የነበሩ የገበያ ትዕዛዞች በመጠንም ሆነ በዋጋ በሚፈለገው ደረጃ ያለመሆናቸው ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ኤክስፖርት የተደረገው ያለቀለት ቆዳ ጠቅላላ የምርት መጠን (56.77 ሚሊዮን ካሬ ጫማ) አምና በተመሳሳይ ወቅት ኤክስፖርት ከተደረገው የምርት መጠን (65.66 ሚሊዮን ካሬ ጫማ) አንፃር ሲታይ በ13.55 በመቶ አካባቢ የመጠን ቅናሽ እንደተመዘገበ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ ከነጠላ የዋጋ አፈፃፀም አኳያ ሲታይ ደግሞ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የተመዘገበው አማካኝ ያለቀለት ቆዳ የኤክስፖርት ምርት ዋጋ (በካሬ ጫማ 1.06 የአሜሪካን ዶላር) አምና በተመሳሳይ ወቅት ከተመዘገበው የነጠላ ዋጋ (በካሬ ጫማ 1.26 የአሜሪካን ዶላር) የ15.87 በመቶ አካባቢ ቅናሽ እንዳለ ያሳያል፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ለተመዘገበው ጉድለት የጎላ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡

ችግሩን ደረጃ በደረጃ ከመፍታት አንፃር እና በተለይም ከአለም ገበያ መቀዛቀዝ ጋር ተያይዞ የሚጠየቀውን ዝቅተኛ ዋጋ እና ጥራት ያለው ምርት ማቅረብ እንዲችሉ በፋብሪካዎች ከማማከር ስራዎች ጉን ለጉን ከልማት አጋሮች ጋር በመሆኑ የምርት ማልማት ስራዎች እንዲከናወኑ

ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ያለቀለት ቆዳ ፍላጐትን ኤክስፖርት ለሚያደርጉ የአገር ውስጥ የቆዳ ውጤቶች ከመጨመር አንፃር የጫማ ፋብሪካዎችን ኤክስፖርት ለማሳደግ የሚደግፍ ኢትዮጵያ ኘሮጀክት ስራ እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ በዚህም በተለይ የአሜሪካ ገበያን ሰብሮ ለመግባት በሚደረገው ጥረት የአሜሪካ የጫማ ገዢዎች ማህበር የስራ አመራሮች ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት እና በአቅርቦት ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ አካላትን በማነጋገር ቀጣይ የስራ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ የሚያስችሉ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

በሌላ በኩል በረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ የደጋ በግ ቆዳ ካለው የተለየ ባህርይ አንፃር የተሻለ ዋጋ እና ገበያ ማግኘት እንዲችል ከልማት አጋር /ጃይካ/ ጋር በመሆን የተጀመረው ጥረትም ቀጣይነት እንዲኖረው ዝርዝር የድጋፍ ተግባራት ታቅደው ከልማት አጋሩ ጋር ለመፈራረም ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን ያሉት የኤክስፖርት ማበረታቻ ስርአቶች ለንዑስ ዘርፉ ኤክስፖርቱን ሊያበረታታ በሚችል እና የጎልዮሽ እና የጐንዮሽ ትስስሩን በማበረታታት ለኤክስፖርት ልማት በሚያመች መልኩ መከናወን እንዲችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስርዓቱን የመከለስ ስራ በማከናወን የመጀመሪያው ረቂቅ ለውይይት በማቅረብ በቀጣይነት ስራው እየተሰራ ይገኛል፡፡

**ለ) የማኔጅመንትና የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት፡-** የክህሎትና የእዉቀት ክፍተቶችን በየደረጃው ከመሙላት አኳያ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የስልጠና ፕሮግራሞችን፤ የኢንዱስትሪ ማማከርና የካይዘን ፍልስፍናን፤ እንዲሁም ሌሎች የአቅም ድጋፎችን ለተመረጡ የቆዳ ፋብሪካዎች ከመስጠትና ከማስረጽ በተጨማሪ በዋናነት የሚስተዋለውን የማጠናቀቅ አቅም ዉስንነት ለማሻሻል ከልማት አጋራት ጋር በመቀናጀት ለመስራት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ እየተከናወኑ ካሉ የአቅም ማጎልበቻ ፕሮጀክቶች አንዱ ደግሞ በእንግሊዝ መንግስት በሚረዳዉ የኢትዮጵያ የግል ድርጅቶች ድጋፍ (PEPE) አንዱ ክንፍ ከሆነዉ የግል ድርጅትቶች አጋር (EnterprisesPartner /EP/) ጋር የተጀመረው የአቅም ግንባታ የፕሮጀክት ሥራ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ በዋነኛነት የሚያተኩረዉ የገበያ ትንበያን በመከተል የተለያዩ ያለቀላቸዉ ምርቶችን የማምረት ዓለም አቀፍ ልምዱና እዉቀቱ ያለቸዉን የቆዳ ኬሚካል አምራችና አቅራቢ ኩባንያዎች በመለየትና ከቆዳ ፋብሪካዎች ጋር በማስተሳሰር ሁለቱንም አካላት የቴክኖሎጂና የገበያ ተጠቃሚ የማድረግ አቅጣጫ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ፋብሪካዎችና ኬሚካል አቅራቢዎች የቴክኖሎጂ ሽግግሩንና የምርት ልማትና የገበያ ትስስሩ በሚከናወንበት ወቅት የሚያስፈልጉ ወጪዎችን በአጋሩ በኩል እንዲሸፈን በማድረግ ትስስሩን የማሳለጥና የማያያዝ (CATALYZING) ሚና እንዲኖረዉ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ በኩል ደግሞ ስራዉን የማስቀጠልና የተገኘዉን ልምድና አሰራር የማቀብ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተደረሰበት ሁኔታም ፕሮጀክቱ ለሚመለከታቸዉ ተሳታፊ አካላት በይፋ (በወርክሾፕ) የተዋወቀ ሲሆን በዚህ ፕሮጀክት

የሚሳተፉት ቆዳ ፋብሪካዎችና የኬሚካል አምራች ኩባንያዎቹም ፍላጎታቸዉን እንዲገልጹ በማድረግ በዉድድር ተለይተዋል፡፡ ፕሮጀክቱ በዋናነት በሀገር ዉስጥ የሚገኙትን ትልልቅና በኤክስፖርት ሥራዉ ላይ በስፋት መሳተፍ የሚችሉትን የጫማና የሌሎች የቆዳ ውጤቶች አምራቾችን ያለቀለት ቆዳ ፍላጎት ባልተቆራረጠ ሁኔታ እንዲሟላ የሚያደርግ ነው፡፡

የፋብሪካዎችን (የቢዝነስ) ማኔጅመንት ዉስንነትን ደረጃ በደረጃ ከማቃለል አኳያ በእቅድና ክትትል፣ በሰዉ ኃይል ልማት፣በሰዉ ኃይል ማበረታቻ፣ በፋይናንስ አጠቃቀም፣ በንብረት አስተዳደርና አያያዝ፣ በኃይል አጠቃቀም፣ በገበያ መረጃና ተያያዥ ድጋፎች፣ በአካባቢ ጥበቃና በሌሎች የማኔጅመንት ስርዓቶች ላይ ለቆዳ ፋብሪካዎች ከሚደረጉ የእለት-ተለት የማኔጅመንት ድጋፎች ባሻገር እነዚህን ድጋፎች ዉጤታማና ተመዛኝ ከማድረግ አኳያ በእነዚህና በሌሎች የማኔጅመንት ስርዓቶች የፋብሪካዎችን ወቅታዊ ደረጃ (COMPETETIVENES RANK) ለይቶ የድጋፍ ዓይነቶችን ለማስቀመጥ የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራም ተከናውኗል፡፡

በሌላ በኩል የጫማ አምራች ኩባንያዎችን በተመለከተ፡- በአብዛኞቹ ዋና ዋና የሀገር ውስጥ የጫማ አምራች ኩባንያዎች የሚስተዋለውን ድርጅታዊ የአመራርና የማኔጅመንት አቅም ውስንነት ተከትሎ የምርትና ምርታማነት አቅምን በሚጠበቀው ልክ አሟጦ ያለመጠቀም ችግር በስፋት ተስተውሏል፡፡ ከዚህ መሠረታዊ ችግር ጋር በተያያዘም ሁሉም የሀገር ውስጥ ዋና ዋና የጫማ አምራች ኩባንያዎች በሚባል ደረጃ አግባብነት ባለው መልኩ በተለያዩ የምርት ግብዓቶች ላይ አስፈላጊውን ወጪ በመቀነስ በምርት ዋጋ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት የሚደረገው ጥረት ያስገኘው ውጤት አነስተኛ ነው፡፡ ይህ ሁኔታም ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ የገበያ ትዕዛዝ ማግኘት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በአጠቃላይ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች የኤክስፖርት አፈፃፀም ዝቅተኛ ሆኗል፡፡

ችግሩን ከመሠረቱ ለመቅረፍ እና የጫማ አምራች ኩባንያዎችን የኤክስፖርት አፈፃፀም ትርጉም ባለው መልኩ ለማሻሻል አምራች ኩባንያዎቹን ከገዢዎች ጋር የማገናኘት ስራ እንዲሰራ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ ገበያዎች በስፋት ሊያስገቡ የሚችሉ ስራዎች በቀጣይነት እተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በዚህም መሰረት ፕሪሚትር ኮንሳልቲንግ እና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሚባል አማካሪ ድርጅት ጋር Made By Ethiopia (MBE) የሚል በገበያ ላይ ፕሮጀክት ተቀርፆ በተመረጡ 10 ጫማ አምራች ኩባንያዎች እና በአማካሪው ደርጅት መካከል አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ እንዲቻል ስምምነት በመፈራረም የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጀምሯል፡፡ በስምምት ሰነዱ መሰረት የመጀመሪያው ቁልፍ ሥራ የተመረጡ ኩባንያዎችን አስፈላጊውን የደህንነትና የምርት ሂደት መስፈርቶችን እንዲያሟሉ በማድረግ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ማድረግ ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የምርት ናሙና በማከናወን ኩባንያዎቹ በማምረት አቅማቸው ልክ ቀጣይነት ያለው የምርት ትዕዛዝ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ

ውጤታማ እንዲሆን በኢንስቲትዩቱ ቢሮ ከማመቻቸት ጀምሮ ረዳት ዲዛይነር እና ገበያውን የሚያስተባብር የገበያ ጥናት ባለሙያ ከመመደብ በተጨማሪ ከምርት ናሙና ልማት ጋር በተያያዘ ሌሎች ግብዓቶችን የማሟላት ሥራ እየተከናወነ ነው፡፡

በተጨማሪም የጫማ አምራች ኢንዱስትሪውን የአቅም አጠቃቀም ሁኔታ በሚጠበቀው ልክ ከማሻሻል አኳያ በበጀት ዓመቱ በተጠናከረ መልኩ በተለያዩ ደረጃዎች የሰው ኃይል ስልጠናን ጨምሮ ሌሎች የኢንዱስትሪ ምክር አገልግሎት ድጋፎች እንዲከናወኑ በማድረግ አፈፃፀምን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል ፡፡ በዚሁ አግባብ በበጀት ዓመቱ በጫማ ምርት የኤክስፖርት ዕቅድ ውስጥ የጎላ ድርሻ ባላቸው ዋና ዋና የሀገር ውስጥ ጫማ አምራች ኩባንያዎች /ጥቁር አባይ፣ ፒኮክ፣ አንበሳ፣ ራምሴ፣ ዋሊያ፣ ሞሐን እና ሞደርንዘጌ/ ውስጥ ከግብዓት ዕቅድ ጀምሮ እስከ ግብይት ባለው የሥራ ሂደት ውስጥ የተሻሻሉ የአሠራር ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግን ጨምሮ ሌሎች የኢንዱስትሪ ምክር አገልግሎት ድጋፍ ሥራዎች በቀጣይነት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

**ሐ) የምርት ግብዓት አቅርቦትና ጥራት ጉድለት፤**

**የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብዓት አቅርቦት ችግር:-** በተለይ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት በሀገር ዉስጥ ያለው የጥሬ ቆዳና ሌጦ የአቅርቦት ሁኔታ ለተመዘገበው የምርትና የኤክስፖርት አፈፃፀም ጉድለት በቀጥታ የጎላ አስተዋፅኦ አልነበረውም፡፡ በአንጻሩ የግብዓቱ አሰባሰብ በተለይም ከፋይናንስና ከገበያ እጥረት ጋር በተያያዘ በርካታ ፋብሪካዎች በበቂ ሁኔታ ግብዓት የመሰብሰብና ምርትና ምርታማነታቸዉን የማስቀጠል ዉስንነት ያጋጠማቸዉና የኤክስፖርት አፈጻጸማቸዉም በከፍተኛ ሁኔታ የወረደ በመሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና ለማቃለል የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ የገበያ ችግሩን ለማቃለል ለአጭርና ለእረጅም ጊዜ እየተተገበሩ ያሉ ሥራዎች ከላይ እንደተገለጸዉ ሆኖ የፋይናንስና ብሎም የግብዓት አሰባሰቡንና አቅርቦቱን ከማሻሻል አኳያ ከኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ጋር ቆዳ አቅራቢዎችና ቆዳ ፋብሪካዎችን በሦስትዮሽ መንገድ በማስተሳሰር ለመፍታት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ጥረት ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ የግብዓት አልሚና ቅራቢ ድርጅቱ ባወጣዉ የአሰራር መመሪያ መሰረት ለማዋዋል ፍላጎት ባለቸዉ በጣም ጥቂት አቅራቢዎችና ቆዳ ፋብሪካዎች መካከል ስራዉ እንዲጀመር የተሞከረ ቢሆንም፤ የቀረበዉ የአሠራር ስርዓት ቆዳ ፋብሪካዎችን ሊስብ ባለመቻሉ የእነዚህን ፋብሪካዎች የፋይናንስ ችግር በማቃልልና ብሎም ምርትና ምርታማነታቸዉን በማሻሻል የኤክስፖርት ስራዉን እንደሚያሳድግ የታመነዉ አሠራር ፈጥኖ ዉጤታማ ባለመሆኑ በሀገር ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች የተመረተዉ በርካታ የቆዳና ሌጦ ግብዓት አሰባሰብ ዝቅተኛ በመሆኑ የግብዓት ብክነት ተከስቷል፡፡

**የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብዓቶች የጥራት ችግር:-** በፋብሪካዎችና በአቅራቢዎች መካከል ተቀራርበዉ እንዲሰሩ የማድረጉ ሥራ ለግብዓት ጥራት መሻሻል ያለዉ ፋይዳ አንድ ጉዳይ ሲሆን፣ የጥሬ ቆዳና ሌጦ የግብይት ሥርዓቱ ማኔጅመንት እንዲተገበር በእንስሳትና አሳ ኃብት ልማት ሚኒስቴር በኩል የተቀረጸዉን ፕሮጀክት ወደ መሬት ለማዉረድና አብሮ ተቀናጅቶ ለመስራት የጋራ ጥረት እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ዉጤታማ ይሆን ዘንድ ለቅንጅቱ የሚረዱ የጋራ ሥራዎች እንደሚኖሩ በመታወቁ ከብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል ጋር በመሆን ሀገራዊ የቆዳና ሌጦ የግድፈት ዳሰሳ ጥናት ተጠናቅቆ በጋራ ለሚመለከታቸዉ የባለድርሻ አካላት ለማቅርብ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

**መ)በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በወቅቱ አለመጠናቀቃቸው፡-** በ2008 በጀት ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ተጠናቀው በበጀት ዓመቱ በኤክስፖርት ረገድ ተጨማሪ አቅም እንደሚሆኑ ታሳቢ ከተደረጉ ፕሮጀክቶች መካከል፡- አንድ የቆዳ ፋብሪካ (ብሉናይል የቆዳ ፋብሪካ)፣ሁለት የጓንት ፋብሪካዎች (ጴብ ኢምፔክስ እና ሊዉሺታኦ ጓንት ፋብሪካዎች)፣ እንዲሁም የኒው ዊንግ አዲስ የጫማ ፋብሪካ የማስፋፊያ ፕሮጀክት /የቀድሞው የአራ ጫማ ፋብሪካ/ ዋነኞቹ ነበሩ፡፡ የተጠቀሱት አዳዲስና የማስፋፊያ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በታቀደው አግባብ ተጠናቀው ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ባለመግባታቸው በንዑስ ዘርፉ የተጨማሪ የምርት አቅምና የኤክስፖርት አፈፃፀም ላይ የራሱን አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡

**ያለቀለት ቆዳ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ፡-**

ብሉናይል የቆዳ ፋብሪካ ፕሮጀክትን በተመለከተም አሁን ላይ በተደረሰበት ሁኔታ ፋብሪካው የግንባታ ሂደቱን ጨርሶ ምርት ለማምረት የተዘጋጀ ቢሆንም፤ የፋብሪካው የፍሳሽ ማጣሪያ ስርዓት ሁለተኛ ደረጃ ብቻ በመሆኑ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው ባስጠናውና በተፈቀደለት መሠረት ብቻ ከዌት ብሉ ጀምሮ መሥራት እንዳለበት አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡ ፋብሪካው ከጥሬ ቆዳ ጀምሮ የመስራት ፍላጎት ስላለው በስምምነቱ መሰረት ይህንንም ለመስራት የሶስተኛ ደረጃ ማጣሪያ እንዲኖረው ግድ ስለሚል ይህንን መስራት እንዲችል የማማከር ስራ እየተሰራ ነው፡፡

ፋብሪካው የሦስተኛ ደረጃ ማጣሪያውን ገንብቶ ተግባራዊ እንዲያደረግ ከሚደረገው ድጋፍ ጎን ለጎን፤ አሁን በደረሰበት የማጣሪያ ስርዓትም ቢሆን የሚፈልገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟላ በከፊል የለፋ የቆዳ (የዌት ብሉ) ግብዓትን በትስስር እንዲያገኝ በማድረግ ፋብሪካው ወደ ምርትና ኤክስፖርት ሥራ እንዲገባ ተደርጎ ለመስራት የሙከራ ምርቶችን እየላከ በመሆኑ በሙሉ አቅሙ ወደ ኤክስፖርት እንዲገባ ከታታ ኩባንያ እና ከአራ ሹ ጋር ስምምነት እየፈጠረ ነው፡፡

በሌላ በኩል በዓመት 60 ሚሊዮን ካሬ ጫማ ያለቀለት ቆዳ የማምረት አቅም ያለዉ **የጆርጅ ግሎሪያ ቆዳ ፋብሪካ** በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የኤክስፖርት እቅድ አፈጻጸም አስተዋጽኦ ታሳቢ

የተደረገ ባይሆንም የኢንቨስትመንት ግንባታ ሥራዉ በእቅዱ መሰረት እየተከናወነ ሲሆን ለ2009 በጀት ዓመት አስተዋጽኦ የሚኖረው ይሆናል፡፡

**የቆዳ ጓንት ኢንቨስትመንትን በተመለከተ፡-**

በተመሳሳይ በጓንት ኢንቨስትመንት ረገድ ከዘገዩ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ***ዴቭ ኢምፔክስ የቆዳ ጓንት ፕሮጀክት ነው***፡፡ ፕሮጀክቱ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በባህርዳር ከተማ የሚገኝ ሲሆን ከክልሉ መንግሥት በተገኘው 8,714 ካሜ ቦታ ላይ እየተገነባ ያለ የጓንት ማምረቻ ፋብሪካ ነው፡፡ የፋብሪካው የፕሮጀክት ግንባታም በዋነኛነት ከሥም ዝውውር ጋር በተያያዘ ለረጅም ጊዜ በመስተጓጎሉ አፈፃፀሙ ከሚጠበቀው ጊዜ በላይ ጊዜ ሊወስድ ችሏል፡፡ በመጨረሻም በቅርቡ በክልሉ ውሳኔ መሠረት ኢንቨስትመንቱ በእህት ኩባንያው /በባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ/ ስም እንዲጠራ መወሰኑን ተከትሎ የፕሮጀክት ሥራው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ አሁን ላይ በተደረሰበት ሁኔታም የፋብሪካው ጠቅላላ ግንባታ ከሚጠበቀው ግማሽ ያህሉ ተፈፅሟል፡፡ ቀሪውን ግንባታ አጠናቆ ወደስራ ለመግባት ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ ያቀረበው የኢንቨስመንት ብድር ጥያቄ በፋብሪካው በኩል ይጠበቁ የነበሩ መረጃዎች ተሟልተው በመግባታቸው ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነትን በማግኘቱ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የፕሮጀክቱን አፈፃፀሙን ለማሻሻል ይሰራል፡፡

***ሊዩ ሺታዎ*** የጓንት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክትን በተመለከተም፡- ኩባንያው መሠረቱን ቻይና ያደረገና በቦሌ ለሚ ቁጥር አንድ ኢንዱስትሪ ፓርክ 5,000 ካ.ሜ የማምረቻ ሼድ ተከራይቶ የጓንት ምርት በማምረት ኤክስፖረት ለማድረግ የተቋቋመ የውጪ ኩባንያ ነው፡፡

ኩባንያው ሙሉ አቅሙን ሲጠቀም በቀን 5,000 የቆዳ ጓንት የማምረት አቅም አለው፡፡ በአሁኑ ወቅት 250 ሠራተኞችን ለሥራ በማሰማራት በፋብሪካው ውስጥ በጨርቅ /የሙከራ/ የጓንት ሥራ ሥልጠና በመስጠት ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በእስካሁኑ ሂደትም በሥልጠና ሂደት የተመረተ /ከጨርቅ የተሠራ/ ከ 50,000 ጥንድ በላይ የሆነን የጓንት ምርት ኤክስፖርት አድርጓል፡፡

**የጫማ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ፡-**

***ከአራ ወደ ኒው ዊንግ*** አዲስ የጫማ ፋብሪካ የተዘዋወረው የቀድሞው የአራ ጫማ ፋብሪካ አሁን ላይ በተደረሰበት ሁኔታም በኒው ዊንግ በኩል በአጭር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም ዝውውሩን ለማጠናቀቅ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ክፍያው እንዲፈፀምና የኩባንያውን የምርትና ኤክስፖርት አፈፃፀም በሚጠበቀው ልክ እንዲሻሻል አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ነው፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በተለይ በጫማ ምርትና ኤክስፖርት ረገድ ትርጉም ያለው ለውጥን እንደሚያመጡ የሚታመንባቸው ትላልቆቹ የሁዋጂያን፣ ጆርጅ ሹ እና የአንበሳ ጫማ የማስፋፊያ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በተቻለ መጠን በታቀደላቸው የጊዜ ገደብ አግባብ ተጠናቀው ወደ

ምርትና ኤክስፖርት ሥራ ይሸጋገሩ ዘንድ በየደረጃው ቀጣይነት ባለው መልኩ ሰፊ የክትትልና ድጋፍ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

***ሁዋጂያን የጫማ ማስፋፊያ የኢንቨስትመንት*** ፕሮጀክትን በተመለከተ፡- በወሩ በተደረሰበት ሁኔታ በዋነኛነት 30,000 ካ.ሜ የሚሆን የማምረቻ ሼድ ግንባታ የመሠረት ሥራ እና ጣራ የማልበስ ስራ ተከናውኖ ተጠናቋል፡፡ ቀሪ የማጠናቀቂያ ስራዎች በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የሚሰሩ ይሆናል፡፡ በግንባታ ሂደትም ውስጥ እያሉ ሰራተኞችን የማሰልጠንና እና በኢንጀክሽን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው የሚመረቱ ጫማዎች ከዱከም ወደ አዲሱ ቦታ ተዛውሮ እየተመረተ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ***የጆርጅ ሹን*** የጫማ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በተመለከተ በተጠናቀቀው ወር መጨረሻ በተደረሰበት ሁኔታ ኩባንያው በተሰጠዉ 25 ሄክታር ቦታ ላይ ለጫማ ማምረቻ የሚዉሉ የሼዶች የግንባታ ሥራ ለመጀመር ሳይቱን አስተካክሎ የቁፋሮ ስራ ጀምሯል፡፡

በተመሳሳይ ***የአንበሳ ጫማ ፋብሪካ*** በቀን 10 ሺህ ጥንድ የሚያመርተው የማስፋፊያ ፕሮጀክትን በተመለከተ በተጠናቀቀው ወር መጨረሻ የፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ዙር የግንባታ ሥራ አስመልክቶ የሁሉም ብሎኮች የስትራክቸራል ስራ ተጠናቆ የሙሌትና የልስን ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ እስካሁን አጠቃላይ የግንባታ ስራው ከ80 በመቶ በላይ ተጠናቋል፡፡ የግንባታዉ ሁለተኛ ዙር የመሠረት ማዉጣት ሥራም አልቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በፕሮጀክቱ ለምርት ሥራ የሚያስፈልጉትን ማሽኖች ለመግዛትና እንዲሁም የሰዉ ኃይል ለመቅጠር የሚያስችሉ የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎችም በመጋቢት ወር መጨረሻ አካባቢ ተጀምረዋል፡፡

***ሠ) የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ*** ፡- በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በአጠቃላይ አዲስ አበባን ጨምሮ በሞጆ አካባቢ በሚገኙ ፋብሪካዎች በ 3,567 ጊዜ ድግግሞሽ ለ 7,866፡27 ሰዓታት ያህል የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ642 ድግግሞሽ እና በ1011:28 ሰዓት ቅናሽ ቢመዘገብም በበጀት ዓመት በተለያዩ ጊዜያት በተለያየ ደረጃ የተስተዋለው የኃይል መቆራረጥና መዋዠቅ ችግር ለተወሰኑ ኩባንያዎች የኤክስፖርት አፈፃፀም ጉድለት የራሱን አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ በተለይ በዋና ዋና ኩባንያዎች የሚከሰተውን የኃይል መቆራረጥ ቸግር በፍጥነት ለማስተካከል እንዲቻልም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎትና በየደረጃው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የጋራ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 2.3. በቀጠይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤

በ2009 በጀት ዓመት በተለየ ትኩረትን ከሚሹ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ዋነኞቹ ናቸው፡-

1. የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውሱንነት፤
2. የገበያ ተያያዥ የዋጋ አፈፃፀም ውሱንነቶች፤
3. የማኔጅመነት አቅም ውሱንነት፤
4. የቴክኒካል /የቴክኖሎጂ/ አቅም ውሱንነት፤
5. በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በወቅቱ አለመጠናቀቅ፤
6. የመንግስት አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ አለመሆን፤

## ክፍል ሦስት፡- ለ2009 በጀት ዓመት የተያዘ የኤክስፖርት ገቢ ግብ፤

በአምራች ኢንዱስትሪው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማትን በማረጋገጡ ሂደት ለልማቱ ምቹ መደላድልን ለመፍጠር ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚደረግላቸው ኢንዱስትሪዎችና ንዑስ ዘርፎች በስትራተጂ ሰነዱ ተለይተዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከተለዩ ንዑሳን ዘርፎች መካከል የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አንዱ እንደመሆኑ መጠን ባለፉት ዓመታት ንዑስ ዘርፉን አስመልክቶ የተቀመጡ የልማት አቅጣጫዎችንና ግቦችን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ በ2009 በጀት ዓመትም በስትራቴጂ ሰነዱ የተመለከተውን የልማት አቅጣጫ የመነሻ መርሆዎች በመከተል ለልማታዊ ባለሀብቱ እየተሰጠ ያለውን ሁሉን አቀፍና የተቀናጀ ድጋፍ አጠናክሮ ከማስቀጠሉ ጎን ለጎን የኪራይ ሰብሳቢነት አማራጮችን በማድረቅ የንዑስ ዘርፉን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል፡፡ ከእስካሁኑ ሂደት በተጨባጭ ከተመዘገቡ ውጤቶችና በአፈፃፀም ሂደት ከተገኙ ተሞክሮዎች በመነሳት በ2009 በጀት ዓመት ከንዑስ ዘርፉ ኤክስፖርት 272.70 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢን ለማሳካት ታቅዷል፡፡

### 3.1. የዕቅዱ ዓላማዎች፣ ግቦች እና ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት፤

#### 3.1.1.ዓላማዎች እና ግቦች፤

**ዓላማ 1፡ በየደረጃው የምርት መጠን፣ ዓይነትና ጥራትን ማሳደግ፤**

1.1 በጫማው ንዑስ የሥራ መስክ አጠቃላይ ዓመታዊ የምርት መጠን በነባር እና አዳዲስ መካከለኛ እና ከፍተኛ፣ በአነስተኛና ጥቃቅን እንዲሁም በጫማ ክላስተሮች 24.75 ሚሊየን ጥንድ ጫማ ላይ ማድረስ፤

1.2 በመካከለኛ እና ከፍተኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪ ደረጃ በሚመደቡት ነባር የጫማ አምራች ፋብሪካዎች በ2008 በጀት ዓመት የተደረሰበትን 57 መቶ አማካኝ ዓመታዊ የአቅም አጠቃቀም 75 በመቶ የአቅም አጠቃቀም እንዲፈጠር ማድረግ፤

1.3 በምርት መጠን ረገድ አነስተኛ (በአማካኝ ከ10 በመቶ አካባቢ) አስተዋፅኦ ያላቸውን ከቆዳ ውጪ ባሉ ግብዓቶች የሚዘጋጁ ጫማዎች ድርሻ 20 በመቶ ማሳደግ፤

1.4 በጫማው ንዑስ የሥራ መስክ በአነስተኛና ጥቃቅን ደረጃ በሚገባ ተደራጅተው ለሚሰሩ ነባርና አዳዲስ የተመረጡ አምራቾች የሚደረገውን ሁለንተናዊ የድጋፍ ሥራ አጠናክሮ በማስቀጠል በ2009 ወደ 5.46 ሚሊዮን ጥንድ ጫማ ማሳደግ፤

1.5 በዳልጋ ከብት ግብዓት ረገድ በ2008 በጀት ዓመት የተደረሰበትን 45 ሚሊዮን ካሬ ጫማ ዓመታዊ ያለቀለት ቆዳ የምርት መጠን በአማካይ በ 3.3 እጥፍ በማሳደግ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ አገራዊ የምርት መጠኑን ወደ 148 ሚሊዮን ካሬ ጫማ ላይ ማድረስ፤

1.6 በነባር የቆዳ ማልፊያና ማለስለሺያ ፋብሪካዎች በ 2008 በጀት ዓመት የተደረሰበትን አማካኝ 40 በመቶ የሌጦና 65 በመቶ የዳልጋ ከብት ቆዳ የአቅም አጠቃቀም በየደረጃው በማሳደግ፤ በ2009 በጀት ዓመት መጫረሻ የአቅም አጠቃቀም ደረጃን በቅደም ተከተል 65 እና 79 በመቶ እና ከዚያ በላይ ማድረስ፤

1.7 በ2008 በጀት ዓመት የተደረሰበትን 1.6 ሚሊዮን ጥንድ ጓንት ዓመታዊ አማካኝ የምርት መጠን በ80 በመቶ በማሳደግ በ2009 አጠቃላይ አገራዊ የምርት መጠኑን 2.9 ሚሊዮን ጥንድ ላይ ማድረስ፤ ይህ ዕድገት ታሳቢ የተደረገው በ2009 በጀት ዓመት ሁለት የጓንት ኢንቨስትመንቶች ተጠናቀው ወደ ኤክስፖርት ይገባሉ ተብሎ ታሳቢ ስለተወሰደ ነው፤

1.8 በመካከለኛ እና ከፍተኛ የማምረቻ ኢንዱስርትሪ ደረጃ በሚመደቡት ነባር የቆዳ ጓንት አምራች ኩባንያዎች በ2008 በጀት ዓመት የተደረሰበትን 85 በመቶ አማካኝ ዓመታዊ የአቅም አጠቃቀም በ2009 በጀት ዓመትም ጠብቀው እንዲሄዱ ማድረግ፤

1.9 በ2008 በጀት ዓመት በተለያየ መልኩ በምርትና ኤክስፖርት ሥራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙ የቆዳ አልባሳት አምራች ድርጅቶችና ኩባንያዎች የተደረሰበትን በቁጥር 1 ሺህ ዓመታዊ የምርት መጠን ከዕጥፍ በላይ በማሳደግ በ2009 አጠቃላይ አገራዊ የምርት መጠኑን በቁጥር 2,290 ላይ ማድረስና፤ ከዚህ የምርት መጠን ውስጥም 7 በመቶ አካባቢ የሚሆነው ከሴንቴቲክ በሚዘጋጁ አልባሳት እንዲሸፈን ማድረግ፤

1.10 በ2008 በጀት ዓመት በተለያየ መልኩ በምርትና ኤክስፖርት ሥራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙ የቆዳ ዕቃዎች አምራች ድርጅቶችና ኩባንያዎች የተደረሰበትን የኤክስፖር ምርት መጠን በቁጥር 31 ሺህ ዓመታዊ የኤክስፖርት ምርት መጠን 88 በመቶ በማሳደግ በ2009 በጀት ዓመት አጠቃላይ አገራዊ የምርት መጠኑን በቁጥር 59 ሺህ ላይ ማድረስና፤ ከዚህ የምርት መጠን ውስጥም 5 በመቶ አካባቢ የሚሆነው ከሴንቴቲክ በሚዘጋጁ ዕቃዎች እንዲሸፈን ማድረግ፤

1.11 በነባር የቆዳ አልባሳት አምራች ድርጅቶችና ኩባንያዎች በ2008 በጀት ዓመት የተደረሰበትን 21 በመቶ ዓመታዊ የአቅም አጠቃቀም በ8 በመቶ በማሳደግ በ2009 38 በመቶ የሆነ የአቅም አጠቃቀምን ማረጋገጥ፤

1.12 በነባር የቆዳ ዕቃዎች አምራች ድርጅቶችና ኩባንያዎች በ2008 በጀት ዓመት የተደረሰበትን 52 በመቶ የአቅም አጠቃቀም በ39 በመቶ በማሳደግ በ2009 በጀት ዓመት 65 በመቶ የአቅም አጠቃቀምን ማረጋገጥ፤

1.13 በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ንዑስ የሥራ መስኮች ረገድ በአነስተኛና ጥቃቅን ደረጃ ተደራጅተዉ ለሚሰሩ ነባርና አዳዲስ አምራቾች የሚደረገዉን ሁለንተናዊ የድጋፍ ሥራ አጠናክሮ በማስቀጠል በ 2008 በጀት ዓመት በተቋማቱ የተደረሰበትን በቁጥር 722 ሺህ የቆዳ አልባሳትና እቃዎች የምርት መጠን በ10 በመቶ በማሳደግ በ2009 መጨረሻ አገራዊ የምርት መጠኑን ወደ 794 ሺህ የምርት መጠን ማሳደግ፤

**ዓላማ 2፡ አዳዲስ ኢንቨስትመንትን ወደ ሥራ በማስገባት ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ ልማትን ማረጋገጥ፤**

1.14 አዳዲስና የማስፋፊያ ኢንቨስትመንቶችን በአግባቡ ተግባራዊ በማድረግ በበጀት ዓመቱ 16.03 ጥንድ ተጨማሪ ጫማን የማምረት አቅም እንዲፈጠር ማድረግ፤

1.15 በዳልጋ ከብት ጥሬ ግብዓት ረገድ አዳዲስ ኢንቨስትመንትን ወደ ንዑስ ዘርፉ ሥራ በማስገባት በ2008 በጀት ዓመት መገባደጃ እንደሚደረስበት የተገመተዉን 3.75 ሚሊዮን የከብት ቆዳ የመንከር አቅምን በላቀ ደረጃ በማሳደግ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ዓመታዊ የመንከር አቅምን ወደ 6.2 ሚሊዮን የዳልጋ ከብት ቆዳ ወይም 148 ሚሊዮን ካሬ ጫማ ያለቀለት ቆዳ ማምረት የሚያስችል አቅም እንዲፈጠር ማድረግ፤

1.16 በ2009 በጀት ዓመት በአዳዲስና የማስፋፊያ ኢንቨስትመንቶች ቢያንስ በቁጥር 60 ሺህ የቆዳና ቆዳ-ነክ አልባሳትና ዕቃዎችን የኤክስፖርት ምርት የማምረት አቅም መፍጠር፤

1.17 በ2009 በጀት ዓመት በአዳዲስና የማስፋፊያ ኢንቨስትመንቶች ቢያንስ በቁጥር 2.8 ሚሊዮን የቆዳ ጓንት የኤክስፖርት ምርት የማምረት አቅም መፍጠር፤

**ዓላማ 3፡ በየደረጃው የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦትን ከማረጋገጡ ጎን ለጎን የተለያዩ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች እንዲከናወኑ በማድረግ ለንዑስ ዘርፉ አስተማማኝ ዕድገት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤**

1.18 በጫማ ንዑስ የስራ ዘርፍ የሚሰጡ የት/ትና ስልጠና ፕሮግራሞችን በክልሎችና በሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች በሚገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተደራሽ በማድረግ በበጀት አመቱ በከፍተኛ የሙያ ደረጃ 587፤ በዝቅተኛና መካከለኛ የሙያ ደረጃ(የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ጨምሮ) 18,437 የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ኃይል ለዘርፉ ኢንዱስትሪ እንዲቀርብ መስራት፤

1.19 በቆዳ አልባሳት ንዑስ የስራ ዘርፍ የሚሰጡ የት/ትና ስልጠና ፕሮግራሞችን በክልሎችና በሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች በሚገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተደራሽ በማድረግ በበጀት አመቱ በከፍተኛ የሙያ ደረጃ 238፤ በዝቅተኛና መካከለኛ የሙያ ደረጃ (የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ጨምሮ) 7,490 የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ኃይል ለዘርፉ ኢንዱስትሪ እንዲቀርብ መስራት፤

1.20 በቆዳ ዕቃዎችና ጓንት ንዑስ የስራ ዘርፍ የሚሰጡ የት/ትና ስልጠና ፕሮግራሞችን በክልሎችና በሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች በሚገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተደራሽ በማድረግ በበጀት አመቱ በከፍተኛ የሙያ ደረጃ 80፤ በዝቅተኛና መካከለኛ የሙያ ደረጃ (የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ጨምሮ) 2,529 የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ኃይል ለዘርፉ ኢንዱስትሪ እንዲቀርብ መስራት፤

1.21 በበጀት አመቱ የዘርፉን ኢንዱስትሪ ባለሙያ የክህሎት ክፍተት መሠረት ያደረጉ የተለያዩ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት 8,341 ባለሙያዎችን በቆዳ፣ በጫማና በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ሙያ ብቃታቸውን ማረጋገጥ፤

1.22 በዘርፉ ኢንዱስትሪዎች በቆዳ እና ቆዳ ዉጤቶች በደጋፊ የስራ መስክ ለ15,329 ዜጎች የስራ ዕድል እንዲፈጠር መስራት፣

1.23 በቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ንዑስ የስራ ዘርፍ የሚሰጡ የት/ትና ስልጠና ፕሮግራሞችን በክልሎችና በሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች በሚገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተደራሽ በማድረግ በበጀት አመቱ በከፍተኛ የሙያ ደረጃ 212፤ በዝቅተኛና መካከለኛ የሙያ ደረጃ (የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ጨምሮ) 6,663 የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ኃይል ለዘርፉ ኢንዱስትሪ እንዲቀርብ መስራት፤

1.24 በበጀት ዓመቱ ለጫማው ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ የሚያስፈልገውን 587 አካባቢ የሚሆን በቀጥተኛ ሞያ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲሁም 18,437 አካባቢ የሚሆን በቴክኒክ እና ሙያ የትምህርት ደረጃ (በዝቅተኛ፣ መካከለኛ እንዲሁም በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራዞችን ጨምሮ) የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት

1.25 በጫማ የሥራ ዘርፍ በአጫጭር ጊዜ ሥልጠና ለ1,644 ለሚሆኑ ሠልጣኞች ሥልጠና መስጠት፤

1.26 በኃይል አጠቃቀም ዙሪያ ፋብሪካዎችን ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለ 4 ፋብሪካዎች የኢነርጂ ኦዲት ማከናወንና የኃይል አጠቃቀማቸውን በ10 በመቶ መቀነስ፣ የተለያዩ አማራጭ ኃይሎችን መለየት፣

1.27 በኤክስፖርት ላይ የተሰማሩ ፋብሪካዎች የኤሌክትሪክ ኃይል እንዳይቆራረጥ በቂ እና አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዲያገኙ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፤

1.28 የዘርፉን ተቋማት አጠቃላይ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግ በምርትና የምርታማነት እንዲሁም በገበያ ላይ ስላለው ሚና የዘርፉን ግንዛቤ ማሳደግ፤

**ዓላማ 4፡ የንዑስ ዘርፉን የቴክኖሎጂ ብቃት፣ የምርታማነትና የምርት ጥራት ደረጃ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ አቅም በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ቀጣይነት ያለው ዘለቄታዊ ልማትን በአግባቡ ማረጋገጥ፤**

4.1 ዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎችን፣ምርታማነት፣ የቴክኖሎጂና የአሰራር ክፍተቶችን በማስተካከል እንዲሁም የምርምር እና የምርት ልማት ስራዎችን ምርት ጥራት ጋር አስተሳስሮ ማከናወን፤

4.2 ዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎችን እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ በምርት አመራረትና በአሰራር ስርዓት ረገድ የሚስተዋሉ የቴክኖሎጂና የአሰራር ክፍተቶችን ማስተካከል፤

4.3 ምርታማነትንና ዓለም አቀፍ የምርት ጥራት ደረጃን የሚያረጋግጡ የምርት ጥራት ፍተሻ እንዲሁም የምርምር፣ የምርት ልማት፣ የምርት ደረጃዎች ዝግጅትና ትግበራ ድጋፍና አገልጎሎትን በቅንጅት በሚፈለገው ልክ ማከናወን፤

4.4 አስፈላጊ የቴክኒካልና ሌሎች የድጋፍ ሥራዎችን በአግባቡ በማከናወን በበጀት ዓመቱ ውስጥ የቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ፋብሪካዎች ዘመናዊ የአካባቢ አያያዝ ስርዓትን በየደረጃው እንዲተገብሩና በአገሪቱ የፀደቀውን የፍሳሽ ቆሻሻ የልቀት ደረጃ እንዲያሟሉ በቅንጅት ድጋፍ ማድረግ፤

4.5 በሞጆ ከተማ ለሚገነባው የጋራ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ግንባታው በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን የተፅዕኖ ጥናት እና የፕሮጀክቱ አዋጭነት ጥናትን በማስገምገም የማጸደቅ ስራ ማጠናቀቅ፤ ለግንባታው የሚያስፈልገውን የገንዘብ ምንጭ ማፈላለግና ማግኘት ፡የሚገነባበት ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መረከብ እና ከቦታው ላይ ለሚነሱ ገበሬዎች የካሳ ክፍያ መፈጸም እንዲሁም የጋራ ማጣሪያ የዲዛይን ሥራዎችን ጨምሮ፤ሌሎች የግንባታና አስተዳደራዊ ሥራዎችን አከናውኖ ማጠናቀቅ፤

4.6 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች አረንጓዴ እና ዘላቂ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

4.7 ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ማድረግ፣ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ከአካባቢ አያያዝ ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት፣

4.8 በቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በፍሳሽ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ትግበራ ላይ የምክርና ቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣

4.9 በኢንቫሮመንታል ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ማንኛውም ከአካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምርምር ፣የአካባቢ ስራ አመራር ስርአት፣ የማጣሪያ ማሽኖች ጥገና፣ ማሽን ኦፐሬሽንና ሌሎች የተግባር ላይ ስልጠና መስጠት፣

4.10 በማምረት ሂደት ላይ ያሉትን የቆዳ ፋብሪካዎች በአካባቢ ጥበቃ ስታንዳርድ መሰረት መስራታቸውን ለማወቅ የኦዲት ስራዎችን ማከናወን፤ በኦዲቱ ውጤት መሰረት አስፈላጊ የቴክኖሎጂ እገዛዎችን ማድረግ፣

4.11 በቆዳው ዘርፍ ያሉትን ፍሳሽ ማጣሪያ እና የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ያሉበትን ደረጃ መፈተሽ፣ መገምገም፣ መፍትሄ መስጠት፣

4.12 ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጂዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉበትን ሁኔታ በመለየት የቤንችማርኪንግ ስራዎችን ማከናወን፣

4.13 በአገሪቱ የተጀመረውን ዘላቂነት ያለው የአረንጓዴ ልማት ለማሳካት በዘርፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አብሮ መስራት፣

4.14 ዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮ /የቤንችማርኪንግ/ ጥናትን በማከናወንና በመተግበር በምርት አመራረትና በአሰራር ስርዓት ረገድ የሚስተዋሉ የቴክኖሎጂና የአሰራር ክፍተቶችን ማስተካከል፤

4.15 ምርታማነትንና ዓለም አቀፍ የምርት ጥራት ደረጃን የሚያረጋግጡ የምርምር፣ የምርት ልማት፣ የምርት ደረጃዎችን የማዘጋጀት እንዲሁም የምርት ጥራት ፍተሻ አገልግሎትንና ድጋፎችን በሚፈለገው ልክ ማከናወን፤

4.16 የዘርፉን የማሽን ጥገና ፍላጎት መለየትና ማጠናቀር፣ በተለዩት ፋብሪካዎች የጥገና ማዕከል እንዲያደራጁ እና የጥገና ስርዓት እንዲኖራቸው ማድረግ፤ ልምዱን መቀመር የምርት ሰዓት ብክነት መቀነስ፤ ለዘርፉ የማሽን ጥገና፣ የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት እና ተከላ እንዲሁም የቴክኒክና ማመከር የድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት፣

**ዓላማ 5፡ በየዓመቱ ቢያንስ በአማካኝ የ44 በመቶ የኤክስፖርት ገቢ እድገትን በማረጋገጥ በልማት ዕቅድ ዘመኑ የንዑስ ዘርፉን የውጭ ምንዛሪ ግኝት መጠንና የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅም በእጅጉ ማሳደግ፤**

5.1 ከጫማው ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ 10.9 ሚሊዮን ጥንድ ጫማ (10.05 ሚሊዮን ጥንድ ሙሉ ጫማ እና 850 ሽህ ጥንድ አፐር) ለውጭ ገበያ በማቅረብ 115 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢን ማሳካት፤

5.2 ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ በማድረግ ለ27,493 ዜጎች ተጨማሪ የስራ እድል እንዲፈጠር ማድረግ፤

5.3 በቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ንዑስ የስራ መስክ በ2008 በጀት ካለቀለት ቆዳ በቀጥታ ኤክስፖርት የተደረሰበትን 77 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጪ ንግድ ገቢ በ2009 በጀት ዓመት ወደ 139.9 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማሳደግ፤

5.4 በ2009 በጀት ዓመት በቁጥር 2.8 ሚሊዮን ጥንድ ጓንትን ኤክስፖርት በማድረግ 14.126 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት፤

5.5 በ2009 በጀት ዓመት በቁጥር 59.26 ሺህ የቆዳ ዕቃዎችን ኤክስፖርት በማድረግ 3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት፤

5.6 በ2009 በጀት ዓመት በቁጥር 2.3 ሺህ የቆዳ አልባሳት ምርት ኤክስፖርት በማድረግ 736 ሺህ የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት፤

**ዓላማ 6፡ ለንዑስ ዘርፉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት የጎላ ፋይዳ ካላቸው የባለድርሻ አካላት ጋር የሚከናወኑ ቅንጅታዊ ሥራዎችን የበለጠ አጠናክሮ በማስቀጠል ለዘርፉ ልማት ራዕይና ዓላማ መሳካት ምቹ ሁኔታን መፍጠር ናቸው፡፡**

6.1 በበጀት ዓመቱ ለምርት ግብዓትነት የሚያገለግሉ የጫማ አክሰሰሪና ኮምፖነንቶች እንዲሁም በሌሎች ግብዓቶች ረገድ የተፋጠነ አቅርቦትና ተያያዥ የአገልግሎት ቅልጥፍና በአግባቡ እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

6.2 በበጀት ዓመቱ የሃገር ውስጥ እና የውጭ ገበያን በማፈላለግ፣ ከገዢ ድርጅቶች ጋር በማስተሳሰር፣ ምርቶችን በማስተዋወቅና የገበያ አቅምን በመገንባት የዘርፉን የወጪ ንግድ ገቢ ግብ በአግባቡ ማሳካት፤

6.3 ንዑስ ዘርፉ ላይ የተጣለውን ግብ ለማሳካት ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት በመስራት በበጀት አመቱ በከፍተኛ የሙያ ደረጃ የሚፈለገውን የሰው ኃይል ለማቅረብ የዘርፉን የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ወደ 5 የዩኒቨርሲቲዎች ተደራሽ ማድረግ፤

6.4 በንዑስ ዘርፉ በዝቅተኛና በመካከለኛ የሙያ ደረጃ የሚፈለገውን የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ኃይል ለማፍራት ከፌዴራል፤ ከክልሎችና ከሁለቱ ከተማ መስተዳድሮች ጋር ቅንጅት በመሰራት በበጀት አመቱ የዘርፉን የቴ.ሙ.ት.ስልጠናን ወደ 10 ተቋማት ተደራሽ ማድረስ፣

6.5 በንዑስ ዘርፉ 11 የዩንቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር ፎረሞችን እንዲሁም በአዳዲስ እና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች የሚፈጠሩ ፋብሪካዎችን በማቀፍ በበጀት አመቱ ብቃት እና ጥራት ያለው የድጋፍ አገልግሎት ለዘርፉ ፋብሪካዎች እንዲሰጡ ማስቻል፡፡

6.6 በበጀት አመቱ ለዘርፉ ትምህርትና ስልጠና የሚያስፈልጉ 220 የቴ.ሙ.ት.ስ. አሰልጣኞችና 40 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን በማፍራት አቅማቸውን ማጎልበት፤

6.7 በዘርፉ በትምህርና ስልጠና ያለውን የመረጃ ፍሰት ክፍተትን ለመሙላት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት በበጀት አመቱ ተደራሽና የተሟላ መረጃ እንዲኖር ማድረግ፡፡

6.8 በ2008 በጀት ዓመት ለቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ፋብሪካዎች የቀረበውን የዳልጋ ከብት ቆዳ በቁጥር 2 ሚሊዮን እና የሌጦ አቅርቦት በቁጥር 19 ሚሊዮን አካባቢ አፈጻጸም በማሻሻል በ2009 በጀት ዓመት የዳልጋ ክብት ቆዳ አቅርቦትን 6.2 ሚሊዮን እና የሌጦ አቅርቦትን 42.27 ሚሊዮን በአጠቃላይ አቅርቦቱ በቁጥር 48.47 ሚሊዮን እንዲደርስ ማድረግ፤

6.9 ለቆዳ ማልፊያና ማለስለሻ ፋብሪካዎች በ2009 በጀት ዓመት ከሚያስፈልገው አጠቃላይ የጥሬ ሌጦ ግብዓት መጠን (42.27 ሚሊዮን በቁጥር) ውስጥ በዓመቱ መጨረሻ በአማካኝ 52.31 በመቶ የሚሆነው ከአገር ውስጥ፤ ቀሪው /47.7 በመቶ የሚሆነው/ ደግሞ ከውጭ አገር እንዲገባ ማድረግ፤

[1] አሁን ባለውነ ባራዊ ሁኔታ በአለም አቀፍ ገበያ መቀዛቀዝ ምክንያት እንዲሁም የቆዳ ፋብሪካዎች የአቅም አጠቃቀም አናሳ መሆን በአገር ውስጥ ያለውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሀብት አሟጦ መጠቀም አለመቻል በማስተዋሉ ከውጪ ማስገባቱ ትኩረት የማይሰጠው ቢሆንም እንሸስትመንቱ ሲነቃቃ ተግባራዊ ለማድረግ የተቀመጠ፤

6.10 በዕቅድ ዘመኑ ለምርት ግብዓትነት የሚያገለግሉ ኬሚካሎች፣ የማሽነሪና መለዋወጫዎች እንዲሁም በሌሎች ግብዓቶች ረገድ የተፋጠነ አቅርቦትና ተያያዥ የአገልግሎት ቅልጥፍና በአግባቡ እንዲረጋገጥ በቅንጅት መስራት፤

6.11 የቆዳ ማልፊያና ማለስለሺያና የጫማ ፋብሪካዎች በላይን አይተምስ ከተለያዩ 162 መለዋወጫዎች ውስጥ ከፍተኛ ፍጆታ ያላቸውን በማስቀደም በአገር ውስጥ እንዲመረቱ፣ የማሽን ማመረትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለጫማ ምርት የተመረቱ 7 ማሽኖችን በተጨማሪ የጫማ እና የቆዳ ውጤቶች 7 ማሽኖችን አምርቶ ወደ ጥቃቅንና አነስተኛ ማስተላለፍና ድጋፍ ማድረግ፣

6.12 ለኢንስቲትዩቱ ሞዴል ፋብሪካዎች ላቦራቶሪ እና ቆሻሻ ማጣሪያ የማሽን ጥገና፣ ተከላ ፣ የቴክኒክና ማማከር የድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት፣

6.13 በበጀት ዓመቱ ለምርት ግብዓትነት የሚያገለግሉ አክሰሰሪና ኮምፖነንቶች፣ ማሽነሪና መለዋወጫዎች እንዲሁም በሌሎች ግብዓቶች ረገድ የተፋጠነ አቅርቦትና ተያያዥ የአገልግሎት ቅልጥፍና በአግባቡ እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

### 3.1.2.ግቦቹን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት፤

በ2009 በጀት ዓመት በዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ቁልፍና አበይት ተግባራት እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

**ሀ/ ቁልፍ ተግባራት፤**

በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ሁሉንም የልማት ኃይሎች በአመለካከት፣በክህሎትና በአቅርቦት አስተባብሮና አቀናጅቶ በመምራት ልማታዊ አስተሳሰብ የበላይነቱን የሚይዝበት የአመራር ዘይቤ ተግባራዊ በማድረግ የዘርፉን ግቦች ማሳካት ነው፡፡

1) ብቁና የሚያሰራ ዕቅድ በማዘጋጀት አመራሩን፣ ፈፃሚውን፣ ባለድርሻ አካላትን በየደረጃው ለተግባር ዝግጁ ማድረግ፤
   - ግምገማዊ ስልጠና መስጠት፣
   - አሳታፊና ጥልቅ ግምገማ ላይ የተመሰረተ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት፣
2) የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች በዕቅድ ውስጥ ተካቶ እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ማድረግ፣
   - የሥርዓተ ፆታና የወጣቶች ጉዳይ ሜንስትሪሚንግን ማጎልበት፤
   - የሴቶችንና የወጣቶችን ሁለንታዊ ብቃት ማጎልበት፤
   - በፆታና በእድሜ የተለየ መረጃ እንዲደራጅና እንዲተነተን ማድረግ፤
   - የግንዛቤና የንቅናቄ ስራን ማከናወን፤
3) አደረጃጀትን የማጠናከር ሥራ መሥራትና የአሠራር ግልጽነትን መፍጠር፤
   - የአመራር አደረጃጀትን መጠናከር፣
   - የፈፃሚ አደረጃጀትን (1 ለ5) ማጠናከር፣

- የኩባንያ አደረጃጀት (የከይዘን ልማት ቡድንን) መጠናከር፣
- የጥራት ሥራ አመራር እና የካይዘን ሥረዓትን አደራጅቶ በመተግበር ግልፅና ፈጣን የአሰራር ሥርዓትን በየደረጃው ተግባራዊ ማድረግ፤

4) የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት በማድረግ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል በፍጥነት ማሟላትና ስልጠና መስጠት፤

5) የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የመተንተን፣ በመረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ወቅታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ማዘጋጀት፤

6) ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም (ማቴሪያልና በጀት) እንዲኖር ማድረግ፤ የመንግስት ሕግና መመሪያዎች በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ከስህተት የፀዳ የኦዲት ሪፖርት ማውጣት፤

7) በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ተልዕኮና ግቦች ላይ የጋራ መግባባት መፍጠርና የዘርፉን ገጽታ መገንባት፤ እንዲሁም ወቅታዊ፣ ትክክለኛና ተዓማኒነት ያለው መረጃ ለሚመለከተው አካልና ለህብረተሰቡ እንዲተላለፍ ማድረግ፤

8) በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ያለውን ኪራይ ሰበሳቢነት አመለካከትና ድርጊት የሚፀየፍ እና አምርሮ የሚታገል አመራርና ፈፃሚ መፍጠር፤

9) በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትና በንዑስ ዘርፉ ተጨማሪ የስጋት አካባቢዎችን መለየት፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶችንና ተግባራትን ለመታገል የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችን መዘርጋት፣ ሕግ፣ ደንብና መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤

10) በመልካም አስተዳደር የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በአግባቡ በመፈተሽ እንዲቀረፉ ማድረግ፣ ለንዑስ ዘርፉ አመራርና ለፈፃሚ ሠራተኞች በመልካም አስተዳደር ላይ ግንዛቤ የማስፋት፣ አፈፃፀሞችን በየጊዜው በመከታተል የማሻሻል ተግባራት ማከናወን፤

11) ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ሥርዓት (BSC) አጠናክሮ መተግበር፤

12) የቁርኝት መረሃ-ግብር ትግበራን በማስቀጠል ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ሥራን መከናወን፤

**ለ/ አበይት ተግባራት፤**

1. **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፤**

- በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስሪ ዘርፍ አዳዲስ የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመመልመልና የመምረጥ፣ በተሟላ ድጋፍ ወደ ፕሮጀክት እንዲገቡ ማድረግ፣
- በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስሪ ዘርፍ ነባር ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ፣ በፕሮጀክት ደረጃ ያሉ ኢንዱስትሪዎች በፍጥነት ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ድጋፍ ማድረግ፣

2. **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤**

- ***የቆዳና የቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም አጠቃቀም ማሳደግ (የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ሙሉ አቅም)፣***

የአቅም አጠቃቀምና የምርታማነት ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችሉ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ። ዋና ዋናዎቹም ሥልጠና መስጠት፣ የምርጥ ተሞክሮ ትግበራ ማከናወን፣ የከይዘን ፍልስፍና መተግበር፣ የቴክኒክና የምክር አገልግሎት የመስጠት፣ የኤነርጂ ኦዲት የማድረግ፣ የኢንጂነሪንግ አቅም የመፍጠር፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወን እና የምርት ደረጃዎች እንዲወጡ የማድረግ ሥራዎች ይከናወናሉ።

- ***የሰው ኃይል ምርታማነት ማሳደግ፣***

ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚያስፈልገውን የስልጠና እና የሰው ኃይል በጥራትና በብዛት ለማቅረብ የእሴት ሰንሰለቱን ተከትሎ የክህሎት ክፍተት መሙያ አጫጭር ሥልጠናዎች ይሰጣሉ። ስልጠናዎቹ በዋናነት በአመራር ክህሎት፣ በጊዜ አጠቃቀም፣ በምርት ዕቅድ አዘገጃጀት፣ በምርት ጥራት አጠባበቅና ቁጥጥር፣ በማሽን ጥገና አመራር፣ በማሽን እንክብካቤና ኦፕሬሽን ላይ የሚያተኩሩ ይሆናሉ።

- ***አዳዲስ ምርቶች* (product diversification) *ለማውጣት ድጋፍ ማድረግ፣***

በንዑስ ዘርፉ አዳዲስ የምርት ዓይነቶች እንዲመረቱ ለማድረግ ከዩኒበቨርሲቲዎች ጋር በመቀናጀት ምርምርና ጥናት፣ የምርት ልማትና ሽግግር ሥራዎች ይከናወናሉ።

- ***የግብዓት አቅርቦትና ግብይትን ማሻሻል፤***

የቆዳና ሌጦ፣ የኬሚካል፣ የአክሰሰሪና ኮምፖነንት የግብዓት አቅርቦት አስተማማኝ የማድረግና የግብይት ስርዓቱን የማሻሻል ስራዎች ይከናወናሉ።

- ***የኤክስፖርት ማበረታቻ ፓኬጅ ድጋፍ፤***

የግብር እፎይታ፣ የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚነት እና ልዩ ልዩ የወጪ መጋራት የድጋፍ ስራዎች ይከናወናሉ፤ የማበረታቻ ስርዓቱ የጥገኝነት አረንቋን በማድረቅ ለልማታዊ ባለሀብቱ የተመቸ ሁኔታ በሚፈጥር መንገድ ይከናወናል።

- ***የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ ድጋፍ፤***

በዘርፉ የተሰማሩ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ቀልጣፋ እና ውጤታማ መንግስታዊ አገልግሎቶች ማግኘታቸውን የማረጋገጥ እና የፋሲሊቴሽን ስራዎች ይከናወናሉ።

3. **ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ አፈፃፀምን የማሳደግ ስራዎች ይከናወናሉ፤**

- **ከክልሎች ጋር በቅንጅት መሥራት፤**

በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ሴክተር በበጀት ዓመቱ የሚተገበሩ የልማትና ድጋፍ ሥራዎች ከክልሎች እንዲሁም ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በቅንጅትና በተናጠል የሚከናወኑ ተግባራት ተለይተዋል፡፡ ዋና ዋና የድጋፍ ስራዎችም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪውን የአመራር ብቃትና ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣ የጥሬ ዕቃና መለዋወጫ ግብዓት አቅርቦት ችግርን መፍታት፣ የኢንዱስትሪውን የእርስ በርስና ከሌሎች ጋር ያለውን ትስስር ማጠናከር ናቸው፡፡

- **ከመንግስታዊ ድጋፍ ሰጪ አካላት ጋር፤**

የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ከሌሎች ድጋፍ ሰጪ የመንግስት ተቋማት የሚፈልገውን ድጋፍ በመሪነት ማስተባበር፣ ድጋፍ ሰጪ አካላት ኢንዱስትሪያሊስቱን በአጋርነት በማየት የሚፈልገውን የመንግስት አገልግሎት ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆኑና ኢንዱስትሪያሊስቱን በግልጽነት ይበልጥ ለመርዳት የጉምሩክና ሎጅስቲክስ አገልግሎት፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ የግብዓት አቅርቦት እና የፋይናንስ አቅርቦት እንዲሟሉ የማድረግ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

## 3.2. የ2009 በጀት ዓመት የወጪ ንግድ ዕቅድ በየምርት ዓይነቱ በመጠን፣ በዋጋ እና ታሳቢ የተደረጉ አንኳር ጉዳዮች፤

<table>
<tr><th>ተ.ቁ</th><th>የምርት ዓይነት</th><th>አጠቃላይ የምርት ማጠን</th><th>አማካኝ ነጠላ ዋጋ</th><th>አጠቃላይ የገቢ ዕቅድ</th><th>በየምርት ዓይነቶቹ ለዕቅዱ ታሳቢ የተደረጉ ዋና ዋናመሠረታዊ ጉዳዮች</th></tr>
<tr><td rowspan="3">1</td><td>የበግ ሌጦ ምርቶች</td><td>39,689,671.72</td><td>2.3</td><td>91,286,244.96</td><td rowspan="4">➢ በተለያዩ የሌጦ ምርቶች ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን አጠቃላይ የምርት መጠን በ2008 የበጀት ዓመት ከተመዘገበው (የ56.77 ሚሊዮን ካሬ ጫማ) የምርትና ኤክስፖርት መጠን በአማካኝ 27.32 በመቶ ማሳደግ፤ በዚህ ሂደትም፡-<br>☞ በጥሬ ሌጦ አቅርቦት ረገድ ከሀገር ውስጥ 22 ሚሊዮን እንዲሁም ከውጭ 20 ሚሊዮን ጥሬ ላጦ እንዲቀርብ አስፈሊጊውን ሁሉ ማከናወን፤<br>☞ ህገ ወጥ (ኮንትሮባንድ) የጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ እንዲቆም እንዲሁም በቆዳ ፋብሪካዎች በኩል በስፋት የሚስተዋለውን የሥራ ማስኬጃ የፋይናንስ አጥረት እንዱቀረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ሁሉ ማከናወን፤<br>☞ በፍየልና በበሬ ቆዳ ረገድ የፋብሪካዎችን የማልፋትና የማጠናቀቅ አቅም ትርጉም ባለው መልኩ በማሳደግ ቢያንስ በአገር ውስጥ የሚገኘው አጠቃላይ የግብዓቱ መጠን አሟጦ መጠቀም፤<br>☞ የምርት ጥራትና ስብጥርን በሚፈለገው ልክ እንዲጨመር በማስቻል በበጀት ዓመቱ በአማካኝ ከተመዘገበው የሽያጭ ዋጋና እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የገበያ ዋጋ አንፃር፡-<br>❖ የበግ ሌጦ ምርቶች ዋጋ በአማካኝ /በካሬ ጫማ/ የ 64.29 በመቶ፤<br>❖ የፊየል ሌጦ ምርቶች ዋጋ በአማካኝ /በካሬ ጫማ/ የ61.29 በመቶ፤ እንዲሁም<br>የበሬ ቆዳ ምርቶች በአማካኝ /በካሬ ጫማ/ የ66.67 በመቶ የዋጋ ጭማሪ እንዲያገኙ አስፈላጊውን የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ማከናወን፡፡</td></tr>
<tr><td>የፊየል ሌጦ ምርቶች</td><td>24,806,044.83</td><td>1.5</td><td>37,209,067.24</td></tr>
<tr><td>የበሬ ቆዳ ምርቶች</td><td>7,789,098.08</td><td>1.4</td><td>10,904,737.31</td></tr>
<tr><td colspan="2">ድምር (1)</td><td>72,284,814.63</td><td></td><td>139,400,049.51</td></tr>
<tr><td rowspan="2">2</td><td>ማኑ ጨማ</td><td>8,421,385.51</td><td>13.00</td><td>102,481,095.26</td><td rowspan="3">➢ በዕቅድ ዘመኑ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የምርት መጠን በብዙ እጥፍ (188.64%) እንዲጨምር አስፈላጊውን ድጋፍና ጥብቅ ክትትል ማከናወን፤በዚህም በተለይ<br>☞ ፋብሪካዎች በአማካኝ 75 በመቶ የማምረት አቅማቸውን እንዲጠቀሙ ማድረግ፤<br>☞ ከታቀደው አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት 37.17 በመቶ የሚሆነው ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ማድረግ፤<br>☞ ህገ-ወጥነትን (የኮንትሮባንድ) ንግድን ለመከላከል አስፈላጊውን ሁሉ ማከናወን፤ እንዲሁም<br>☞ አዳዲስና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በቶሎ ወደ ምርትና ኤክስፖርት ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል፤<br>የምርት ጥራትና ስብጥርን በሚገባ በማሳደግ አንድ ጥንድ ሙሉ ጫማ በአማካኝ 13 የአሜ.ዶ እንዲሁም አንድ ጥንድ የአፐር ምርት በአማካኝ በ7 የአሜ.ዶ እንዲሸጥ አስፈላጊውን የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ማከናወን፡፡</td></tr>
<tr><td>የጫማየ ላይኛው ክፍል</td><td>848,738.34</td><td>7.00</td><td>12,925,544.74</td></tr>
<tr><td colspan="2">ድምር (2)</td><td>9,270,123.85</td><td></td><td>115,419,180.01</td></tr>
<tr><td rowspan="2">3</td><td>ዳንት</td><td>በጥንድ</td><td>በአሜ ዶላር</td><td>በአሜዶላር</td><td rowspan="3">➢ በቆዳ ምርትና ኤክስፖርት ረገድ በተለይ በ2009 በጀት ዓመት ለነባሮቹ ከሚደረገው ሁለንተናዊ ክትትልና ድጋፍ ሥራ ጎን ለጎን፤ መስመር ላይ የሚገኙ አዳዲስ አምራቾችን ወደ ምርትና ኤክስፖርት ሥራ በማስገባት በዕቅድ ዘመኑ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የምርት መጠን በ2008 በጀት ዓመት ከተደረሰበት /1.2 ሚሊዮን ጥንድ/ በ 135 በመቶ ለማሳደግ ሁለንተናዊ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡</td></tr>
<tr><td>የቆዳ ዳንት ምርት</td><td>2,826,937.28</td><td>5.00</td><td>14,134,686.40</td></tr>
<tr><td colspan="2">ድምር (3)</td><td>2,826,937.28</td><td></td><td>14,134,686.40</td></tr>
<tr><td rowspan="2">4</td><td>የቆዳ ዕቃዎች</td><td>በቁጥር</td><td>በአሜ ዶላር</td><td>በአሜዶላር</td><td rowspan="6">➢ በቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ምርትና ኤክስፖርት ረገድ በበጀት ዓመቱ የተያዘውን ዕቅድ በአግባቡ ከማሳካት አንፃር አሁን በሥራው ላይ ተሰማርተው ከሚገኙ ኩባንያዎችና አምራች ያልሆኑ ላኪዎች በተጨማሪ ለተመረጡ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በኤክስፖርት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ፤</td></tr>
<tr><td>የቆዳ ዕቃዎች</td><td>199,792.00</td><td>15</td><td>2,996,880.00</td></tr>
<tr><td colspan="2">ድምር (4)</td><td>353,964,600.00</td><td></td><td>2,996,880.00</td></tr>
<tr><td rowspan="2">5</td><td>የቆዳ አልባሳት</td><td>በቁጥር</td><td>በአሜ ዶላር</td><td>በአሜዶላር</td></tr>
<tr><td>የቆዳ አልባሳት ምርት</td><td>6,349.00</td><td>118.00</td><td>749,182.00</td></tr>
<tr><td colspan="2">ድምር (5)</td><td>6,349.00</td><td></td><td>749,182.00</td></tr>
</table>

| ጠቅላላ ድምር | 272,700,000.00 |
|---|---|

## 3.3. ዝርዝር የኤክስፖርት መጠንና የገቢ ግብ ዕቅድ፤

| የ ምርት ዓይነ ት | | | የ 2009 ጠቅላላ ዓመታዊ ዕቅድ | የ ጊዜ ሰሌዳ | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ሀምሌ | ነ ሀሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | የ ካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ |
| ያለቀለት ቆዳ | | የ ኤክስፖርት ምርት ማጠን /በሺህ ካሬ ጫማ | 72,284.81 | 6,023.73 | 4,468.10 | 4,468.10 | 6,023.73 | 4,468.10 | 4,986.65 | 4,986.65 | 4,986.65 | 6,023.73 | 8,131.34 | 8,594.94 | 8,641.29 |
| | | የ ኤክስፖርት ማጠን /በሺህ የ አሜሪካን ዶላር/ | 139,400.05 | 11,616.67 | 8,616.67 | 8,616.67 | 11,616.67 | 7,947.33 | 9,616.67 | 9,616.67 | 9,616.67 | 11,616.67 | 15,681.16 | 16,575.20 | 16,664.60 |
| ጫማ | ማሉ ጫማ | የ ኤክስፖርት ምርት ማጠን /በሺህ ጥንድ/ | 8,421.39 | 701.78 | 471.01 | 471.01 | 471.01 | 701.78 | 547.93 | 547.93 | 547.93 | 701.78 | 1,014.43 | 1,083.20 | 1,090.08 |
| | | የ ኤክስፖርት ማጠን /በሺህ የ አሜሪካን ዶላር/ | 109,478.01 | 9,123.17 | 6,123.17 | 6,123.17 | 6,123.17 | 8,721.56 | 7,123.17 | 7,123.17 | 7,123.17 | 9,123.17 | 13,187.66 | 14,081.70 | 14,171.10 |
| | አ ፐር | የ ኤክስፖርት ምርት ማጠን /በሺህ ጥንድ/ | 848.74 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 | 70.73 |
| | | የ ኤክስፖርት ማጠን /በሺህ የ አሜሪካን ዶላር/ | 5,941.17 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 | 495.10 |
| የ ጫማድምር | | የ ኤክስፖርት ምርት ማጠን /በሺህ ጥንድ/ | 9,270.12 | 772.51 | 541.74 | 541.74 | 541.74 | 772.51 | 618.66 | 618.66 | 477.20 | 772.51 | 1,085.16 | 1,153.93 | 1,160.81 |
| | | የ ኤክስፖርት ማጠን /በሺህ የ አሜሪካን ዶላር/ | 115,419.18 | 9,618.27 | 6,618.27 | 6,618.27 | 6,618.27 | 9,216.66 | 7,618.27 | 7,618.27 | 7,618.27 | 9,618.27 | 13,682.76 | 14,576.80 | 14,666.20 |
| የ ቆዳ ጓንት | | የ ኤክስፖርት ምርት ማጠን /በሺህ ጥንድ/ | 2,826.94 | 141.35 | 141.35 | 424.04 | 452.31 | 452.31 | 282.69 | 141.35 | 141.35 | 141.35 | 197.89 | 169.62 | 141.35 |
| | | የ ኤክስፖርት ማጠን /በሺህ የ አሜሪካን ዶላር/ | 14,134.69 | 706.73 | 706.73 | 2,120.20 | 2,261.55 | 2,261.55 | 1,413.47 | 706.73 | 706.73 | 706.73 | 989.43 | 848.08 | 706.73 |
| የ ቆዳ ዕቃዎች | | የ ኤክስፖርት ምርት ማጠን /በሺህ ቁጥር/ | 199.79 | 9.99 | 9.99 | 29.97 | 31.97 | 31.97 | 19.98 | 9.99 | 9.99 | 9.99 | 13.99 | 11.99 | 9.99 |
| | | የ ኤክስፖርት ማጠን /በሺህ የ አሜሪካን ዶላር/ | 2,996.88 | 149.84 | 149.84 | 449.53 | 479.50 | 479.50 | 299.69 | 149.84 | 149.84 | 149.84 | 209.78 | 179.81 | 149.84 |
| የ ቆዳ | | የ ኤክስፖርት ምርት ማጠን /በሺህ ቁጥር/ | 6.35 | 0.32 | 0.32 | 0.95 | 1.02 | 1.02 | 0.63 | 0.32 | 0.32 | 0.32 | 0.44 | 0.38 | 0.32 |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **አልባሳት** | የኤክስፖርት ማጠን /በሺህ የአሜሪካን ዶላር/ | **749.18** | 37.46 | 37.46 | 112.38 | 119.87 | 119.87 | 74.92 | 37.46 | 37.46 | 37.46 | 52.44 | 44.95 | 37.46 |
| **ጠቅላላ የኤክስፖርት ገቢ ዕቅድ /በሺህ የአሜሪካን ዶላር/** | | **272,699.98** | **22,128.97** | **16,128.97** | **16,846.11** | **21,095.86** | **20,024.92** | **19,023.02** | **18,128.97** | **22,128.97** | **22,128.97** | **30,615.56** | **32,224.83** | **32,224.83** |